የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 28
ADDIS ABABA 24th January 2003

ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፫/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የኢትዮጵያ ልማት ባንክን እንደገና ለማቋቋም የወጣ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገጽ ፪ሺ፸

CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 83/2003
Development Bank of Ethiopia Re-establishment
Council of Ministers Regulations ............ Page 2070

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፫ /፲፱፻፺፭
### የኢትዮጵያ ልማት ባንክን እንደገና ለማቋቋም የወጣ
### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አዋጅ ቁጥር ፩/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፸፯/፲፫/ እና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፮/፩/ሀ/ መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ልማት ባንክን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፹፫/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· እንደገና መቋቋም

፩· የኢትዮጵያ ልማት ባንክ /ከዚህ በኋላ "ባንኩ" እየተባለ የሚጠራው/የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ እንደገና ተቋቁሟል።

፪· የገንዘብና የባንክ ሥራን የሚመለከቱ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆኖ ባንኩ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል።

፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግሥት የሚሰየም አካል የባንኩ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO 83/2003
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE DEVELOPMENT BANK OF ETHIOPIA

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 77(13) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1/1995 and Article 5 of proclamation No. 4/1995 provided for the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and Article 46 (1) (a), of the Public Enterprise Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

   *These Regulations may be cited as the "Development Bank of Ethiopia Re-establishment Council of Ministers Regulations No 83/2003."*

2. *Re-establishment*

   1) There is hereby re-established the Development Bank of Ethiopia (hereinafter called the "Bank") as a public enterprise.
   2) Withoutprejudice to the applicability of Monetary and Banking laws, the Bank shall be governed by the Public Enterprise Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

   A body to be designated by the Government shall be the supervising authority of the Bank.

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል። እንደ አስፈላጊነቱም በማንኛውም ስፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭· ተልዕኮ

ባንኩ የተቋቋመው የሃገሪቱን ልማት ለማፋጠን የሚያስችል የልማት ብድር አገልግሎት ለመስጠት ነው።

፮· የባንኩ ተግባርና ኃላፊነት

፩· የኢንቨስትመንት ብድር የአጭር ጊዜ ብድርን ጨምሮ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላላቸውና ውጤታማ ለሆኑ ፕሮጀክቶች መስጠት፤
፪· ከአገር ውስጥና ከውጭ ምንጭ ለልማት የሚውል ገንዘብ ማሰባሰብ፤
፫· የአደራ ገንዘብ ማስተዳደር፤
፬· የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ በኢንቨስትመንት መሳተፍ፤
፭· ለተበዳሪዎቹ የሃገር ውስጥና የውጭ ሃገር የባንክ አገልግሎት መስጠት፤
፮· የጊዜ ገደብ ያለው ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፤
፯· ለብድሮችና ለሌሎች መሰል የገንዘብ ግዴታዎች ዋስ መሆን፤
፰· በኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ተከፋይ የሚሆኑ የሐዋላ ወረቀቶች፣ የገንዘብ ሰነዶችና የተስፋ ሰነዶች ማውጣት፣ መቀበል፤ በቅናሽ መውሰድ፣ መግዛትና መሸጥ፣
፱· ቦንድ ማውጣትና መሸጥ፤
፲· እንደ ባለአደራ ወይም እንደ ንብረት ተቀባይና ጠባቂ መስራት፤
፲፩· የቴክኒክና የሥራ አመራር ምክር አገልግሎት መስጠት፤
፲፪· በአገር ውስጥና በውጭ ባንኮች ሂሣብ መክፈትና ማንቀሳቀስ፤
፲፫· ሌሎች የተለመዱ የልማት ባንክ ሥራዎችን ማከናወን።

፯· ካፒታል

ለባንኩ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፮፻ ሚሊዮን /ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር/ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ብር ፬፻፹ ሚሊዮን /አራት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን ብር/ የተከፈለ ካፒታል ይሆናል።

፰· ኃላፊነት

ባንኩ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፱· ባንኩ የሚቆይበት ጊዜ

ባንኩ ላልተወሰነ ጊዜ እንደገና ተቋቁሟል።

፲· መብትና ግዴታዎችን ለማስተላለፍ

በደንብ ቁጥር ፪፻/፲፱፻፹፮ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ልማት ባንክ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለባንኩ ተላልፈዋል።

፲፩· ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Bank shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Mission*

*The Bank is established to accelerate the Country's development through the provision of development credits.*

6. *Purpose*

*The purpose for which the Bank is re-established are:-*

1) *to provide investment credits including short-term loans to viable projects that will contribute to the country's economic development.*
2) *to mobilize funds from sources within or outside the country;*
3) *to manage funds entrusted to it;*
4) *to participate in equity investment;*
5) *to provide domestic and foreign banking services to its borrowers;*
6) *to accept time deposits;*
7) *to guarantee loans and other financial obligations;*
8) *to draw, accept, discount, buy and sell bills of exchange, drafts and promissory notes payable within or outside of Ethiopia;*
9) *issue and sell bonds*
10) *to act as a trustee;*
11) *to provide technical and managerial services;*
12) *to open and oeperate bank accounts, with banks and banking correspondents in Ethiopia or abroad;*
13) *to engage in such other activities as is customarily carried out by development banks.*

7. *Capital*

To authorized capital of the Bank is Birr 600,000,000,– (Six Hundred Million Birr) of which Birr 480,000,000 (Four hundred eighty million birr) shall be paid up.

8. *Liability*

The Bank shall not be liable beyond its total assets.

9. *Duration*

The Bank is re-established for an indefinite duration.

10. *Transfer of rights and obligations*

The rights and obligations of Development Bank of Ethiopia established under Regulations No. 200/1994 are hereby transferred to the Bank.

11. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of their publications in the Federal Negarit Gazetta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of January 2003.

MELLES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE